# እንኳን ወደ እንግሊዝ ሃገር በደህና መጡ

North East Migration Partnership




በእንግሊዝ ሃገር ዉስጥ የፖሊሶች ስራ የሰዎችን መብት ማስከበር እና ህግን ማስጠበቅ ነዉ። በእንግሊዝ ዉስጥ ህግን ማክበር በጣም አስፈላጊ ነዉ ፤ እናም ሁሉም ሰዉ ህጉን ማክበር አለበት። ህግን መጣስ መዘዝ አለዉ። ቅጣት ሊጣልቦት ወይም ወደ እስር ቤት ሊገቡ ይችላሉ። ወደፊትም የእንግሊዝ ዜግነት ማመልከቻዎንም ሊጎዳ ይችላል።

ፖሊሶች ህጉን የማስጠበቅ፣ ወንጀልን የመከላከል፣ ህግ ተላላፊዎችን ወደ ፍትህ የማቅረብ፣ ሰላም እና ፀጥታን የማስከበር ፣ እናም ማህበረሰቡን የመርዳት እና የማረጋጋት ሃላፊነት አለባቸዉ። እርሶን ለመርዳት እና ለማገዝ ያሉ ስለሆነ ወንጀል ከተፈፀመቦት ፣ ወንጀል ሲፈፀም ካዩ ወይም ሌላ እርዳታ ከፈለጉ ለምሳሌ አቅጣጫ ከጠፋቦት ቀረብ ብለዉ ለመጠየቅ አይፍሩ።

በሌላ ሃገሮች የሚፈቀዱ ነገር ግን በእንግሊዝ ሃገር ዉስጥ ተቀባይነት የሌላቸዉ ነገሮች እንዳሉ ማወቅ ያስፈልጋል ፤ ለእንግሊዝ ሃገር ህጎች ተገዝቶ መኖር የእርሶ ሃላፊነት ነዉ። እንዲሁም በሌላ ሃገሮች የማይፈቀዱ ነገር ግን በእንግሊዝ ሃገር ዉስጥ ህጋዊ የሆኑ ነግሮች እንዳሉም ማስተዋል ያስፈልጋል።

## የቤት ኑሮ በእንግሊዝ ሃገር



ጥሩ ጉርብትና እንዲኖሮት ምሽት እና በጣም ጠዋት ላይ ድምፃችን ይቀንሱ። ድግስ የሚያዘጋጁ ወይም ብዙ ሰዎችን ወደቤትዎ የሚጠሩ ከሆነ ለጎረቤቶችዎ ያስታዉቁ። መስኮቶች እና በሮችን በሁሉም ሰአታት መቆለፍ እና ብስክሌቶችን እና የኤሌክትሮኒክ እቃዎችን ደህንነታቸዉ በተጠበቁ ቦታዎች ላይ ማስቀመጥ ብልህነት ነዉ። በቤትዎ ዉስጥ ቴሌቪዥን ማየት ከፈለጉ የቲቪ ፈቃድ ያስፈልጎታል።

በየትኛዉ ቀን ቆሻሻ ማዉጣት እንዳለቦት ይወቁ። ቆሻሻው ከተነሳ በኋላ የቆሻሻ መጣያ ገንዳዉን መልሰዉ ያስገቡ። በተለያዩ ቦታዎች ለተለያዩ የቆሻሻ አይነቶች (ለምሳሌ ለሪሳይክሊንግ) የተለያዩ የቆሻሻ መጣያ ገንዳዎች፣ ሳጥኖች እና ማጠራቀሚያ ዘምቢሎች አሉ።

በእንግሊዝ ሃገር ዉስጥ ሁሉም ሰዉ አካባቢዉን የመንከከባከብ ሃላፊነት አለበት። የህዝብ የሆኑ ቦታዎች ላይ እና መንገዶች ላይ ቆሻሻ መጣል የለበትም እንዲሁም ተገቢ የሆኑትን የቆሻሻ እና የሪሳይክሊንግ ገንዳዎችን መጠቀም አለቦት። ቆሻሻን ወደ ዉጪ መወርወር/መጣል/ማስቀመጥ በህግ ያስቀጣል ይህም ማስቲካን፣ ሲጋራን እና ጥራጥሬዎችን ይጨምራል። ይህ ሊተሪንግ ይባላል እና ቅጣት ሊያስጥልቦት ይችላል። በተጨማሪም መንገድ ላይ እና ሌላ የህዝብ ቦታዎች ላይ መትፋት ተቀይነት የሌለዉ ስነ ምግባር ነዉ ቅጣትም ሊያስጥልቦት ይችላል።

በእንግሊዝ ዉስጥ በእግረኛ መንገድ ላይ ሳይክል መንዳት ክልክል ነዉ ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።። ለእርሶ እና ለሌሎች ደህንነት ሲባል ማታ ማታ ሳይክል ሲነዱ የፊት እና የኋላ መብራቶችን ያብሩ።



## እንግሊዝ ሃገር ዉስጥ መኪና መንዳት




የመንጃ እና የአሽከርካሪ ፈቃድ ኤጀንሲ፣ ዲ.ቪ.ኤል.ኤ ተብሎ የሚታወቀዉ ኤጀንሲ እንግሊዝ ዉስጥ ለመኖር ህጋዊ ፈቃድ ከሌሎት የመንጃ ፈቃድ ሊሰጦት አይችልም። ይህ ሃገሪቷ ዉስጥ ለመቆየት ፈቃድ የሌላቸዉን ሁሉ ያጠቃልላል። ዲ.ቪ.ኤል.ኤ እንግሊዝ ሃገር ዉስጥ ለመቆየት ፈቃድ የሎትም ብሎ ካመነ የመንጃ ፈቃዶን የመሰረዝ መብት አለዉ። ዲ.ቪ.ኤል.ኤ መንጃ ፈቃዶ መሰረዙን የማሳወቅ ግዴታ የለበትም። ይህ ማለት በህገ ወጥ መንገድ መኪና እያሽከረከሩ መሆኑን ፖሊስ እስኪያስቆሞ ድረስ ላያዉቁ ይችላሉ ማለት ነዉ።

ከሚኖሩበት ሃገር የተሰጦት የታደሰ የመንጃ ፈቃድ ካሎት፣ እዚህ አገር ከመጡበት ቀን ጀምሮ ለ12 ወራት ያክል መንዳት ይፈቀድሎታል። ነገር ግን ዲ.ቪ.ኤል.ኤ ጋር ማረጋገጥ አለቦት። ከ12 ወር በኋላ የብሪቲሽ መንጃ ፈቃድ ማዉጣት አለቦት። የብሪቲሽ መንጃ ፈቃድ ከመያዞት በፊት የመኪና ፈተናዉን ለማለፍ የመኪና ትምህርት መዉሰድ ሊኖርቦት ይችላል። በእንግሊዝ ሃገር ዉስጥ መኪና ለመንዳት በትንሹ 17 አመት መሆን አለቦት።

የታደሰ የመንጃ ፈቃድ በህጋዊ መንገድ መኪና ለመንዳት ከሚያስፈልጉት ነግሮች ዉስጥ አንዱ ሲሆን፣ በተጨማሪም የሚከተሉት ያስፈልጎታል

- የመንዳት ሽፋን የሚሰጥ የኢንሹራንስ ሰርተፊኬት
- መኪናዉ የመንገድ ግብር ያስፈልገዋል
- መኪናዉ አመታዊ የሆነዉን እና ኤም.ኦ.ቲ (MOT) የሚባለዉን የመንገድ ደህንነት ግምገማ ማለፍ ያስፈልገዋል

ከጓደኛ የተዋሱትን መኪና ሲነዱ ጥንቃቄ ያድርጉ ምክያቱም ማንኛዉንም ተሽከርካሪን የታደሰ የመንጃ ፈቃድ፣ የኢንሹራንስ ሰርተፊኬት፣ የመንገድ ግብር እና ኤም.ኦ.ቲ ሰርተፊኬት ሳይኖረዉ መንዳት ጥፋት ነዉ። ፖሊሶች ማንኛዉንም ነጂ የማስቆም መብት አላቸዉ። ማለትም ምንም እንኳን ጥፋት አጥፍተዋል ብለዉ እንኳን ባያስቡም የማስቆም መብት አላቸዉ። ፖሊስ ሲያስቆሞት የመንጃ ፈቃዶትን፣ የኢንሹራንስ እና ኤም.ኦ.ቲ ሰርተፊኬቶትን እንዲያሳዩ ሊጠይቁ ይችላሉ። እነዚን ዶኪመንቶች ካልያዙ ዶክመንቶቹን በሰባት ቀናት ዉስጥ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ማቅረብ አለቦት። በሰባት ቀናት ዉስጥ እነዚህን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ካላቀረቡ ህግ በመጣሶ ወደ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ይችላሉ። ፖሊስ ኢንሹራንስ የሎትም ብሎ ካሰበ ኢንሹራንስ እንዳሎት እስከሚያረጋግጡ ድረስ መኪናዎን ሊወስድ ይችላል።

መኪና ለመንዳት ካሰቡ የሚከተሉት ነገሮች ጥፋት መሆናቸዉን ማወቅ አለቦት

- በተለያዩ መንገዶች ላይ ከተፈቀደዉ የፍጥነት መጠን በላይ መንዳት። እንግሊዝ ዉስት የፍጥነት መጠኑ የሚለካዉ በማይል እንጂ በኪሎ ሜትር አይደለም።
- መጠጥ ወይም አደንዛዥ እፅ ወስዶ ህዝብ በሚተላለፍበት መንገድ ወይም ቦታ ላይ ማሽከርከር
- መኪና እየነዱ ተንቀሳቃሽ ስልክ መጠቀም
- ልጆች መኪና ዉስጥ እያሉ ማጨስ
- ለእያንዳንዱ ተጓዥ ቀበቶ መኖር አለበት እናም ሁሉም ቀበቶ ማሰር አለበት
- አሽከርካሪዉ ከ14 አመት በታች ለሆኑ ልጆች ቀብቶ ማሰሪያ ስለመኖሩ፣ ከፍ የሚያደርግ መቀመጫ (ቡስተር ሲት)እና የመኪና መቀመጫ (ካር ሲት) ስለመኖሩ ሃላፊነት ይወስዳል።

## ስራ በእንግሊዝ ሃገር




ጥገኝነት ጠያቂዎች እንዲቆዩ ፈቃድ እስከሚሰጣቸዉ ድረስ ስራ መስራት አይፈቀድላቸዉም። ለቅድሚያ ውሳኔዉ ከ12 ወራት በላይ ከጠበቃችሁ፣ የስራ ፍቃድ እንዲሰጥ ማመልከት ይችላሉ። የስራ ፈቃድ ከተሰጦት የግል ስራ መስራት አይፈቀድሎትም ፣ መስራት የሚፈቀድሎት የተቀጣሪ እጥረት አለባቸዉ ተብለዉ በእንግሊዝ ቪዛ እና ኢሚግሬሽን የተመረጡ ስራዎችን ብቻ ነዉ። መስራት ሳይፈቀድሎት ስራ ከሰሩ ገቢዎት እና ንብረቶት በመንግስት ሊወሰድ ይቻላል። ሊታሰሩ ወይም ከሃገር ሊባረሩ የሚችሉበት አጋጣሚም አለ።

የስራ እድል እንዳለ አስመስለዉ የሚቀርቧችሁን ሰዎች ተጠንቀቁ፤ የመስሪያ ፈቃድ እንደሌሎት አውቀዉ ለወንጀል መጠቀሚያ ሊያደርጎት እናም በግድ ስራ እንዲሰሩ በማስፈራራት፣ በሃይል ፣ በመዋሸት ወይም ሃይላቸዉን አላግባብ ሊጠቀሙቦት ይችላሉ። ለምሳሌ ስለግል ህይወቶ የሚያዉቁትን መረጃ ተጠቅመዉ ቤተሰቦችን በማስፈራራት እና ስለኢሚግሬሽን ያሎትን ፍርሃት ተጠቅመዉ እርሶን ለመቆጣጠር ይችላሉ። በእንግሊዝ ሃገር ይህ ሁኔታ አዲሱ ባርነት ተብሎ ይታወቃል ፤ የሚያቁት ሰዉ ወይም እርሶ የዚህ ጥቃት ሰለባ ከሆኑ እባኮን ፖሊስን ያናግሩ። የጥገኝነት ማመልከቻዎ ዉሳኔ እስከሚያገኝ ግዜ ስለሚያስፈልገዉ፣ መስራት ባይችሉም ትርፍ ጊዜዎን የአካባቢዉ ማህበርተሰብ አካል መሆን፣ የተለያዩ ነገሮች ላይ መሳተፍ፣ ሰዎችን መተዋወቅ እና የበጎ ፈቃደኛ አግልግሎትን ማከናወን ይጠቀሙበት።



### ከወሲብ ጋር በተገናኘ የእንግሊዝ ህግ

እንግሊዝ ሃገር ዉስጥ ከማንም ሰዉ ጋር ካለፈቃድ ወሲብ መፈፀም ጥፋት ነዉ (ይህ ማለት ሁለቱም ሰዎች ከተስማሙ እና ለመወሰን ነፃነት ካለ ነዉ)። አላስፈላጊ ንክኪዎችን ለምሳሌ መነካካት፣ መሳም እና ማንኛዉንም ሰዉ መያዝ። ይህ ሚስቶችን፣ ሴት ጓደኞችን እና አጋሮችን ያካትታል።

አንድ ሰዉ ከሰከረ ወይም በእፅ ከፈዘዘ ፈቃድ መስጠት እንደማይችል ማወቅ ያስፈልጋል። የሰከረ ወይም በእፅ ከፈዘዘ ሰዉ ጋር ምን እየተፈጠረ እንደሆነ ሳያዉቁ እና ፈቃድ መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ምንም አይነት ወሲባዊ ድርጊት ቢፈፅሙ እንደ አስገድዶ መድፈር ነዉ የሚቆጠረዉ።



ከ18 አመት በታች የሆኑ ልጆችን ፖርኖግራፊ ፎቶ ይዞ መገኘት ጥፋት ነዉ፣ ተንቀሻቃሽ ስልክ ላይ መያዝንም ያካትታል። ከ18 አመት በታች የሆነ ልጅ ፖርኖግራፊ ፎቶ ከተላከሎት ለማንም መልሰዉ እንዳይልኩት፣ ፎቶዉን ያጥፉት ከዚያ ሰው ጋርም ግንኙነቶን ያቁሙ። አንድ ሰዉ በደል እየደረሰበት ነዉ ብለዉ ካሰቡ ለፖሊስ ያመልክቱ።

ወንዶችም ሆነ ሴቶች ከ16 አመት በታች ከሆነ ሰዉ ጋር ወሲብ ከፈፀሙ ጥፋት ነዉ ፤ ልጆቹ ቢስማሙም። ክለብ ዉስጥ ወይም ባር ዉስጥ ስለተዋወቋቸዉ ብቻ ከ16 ኣመት በላይ ናቸዉ ብለዉ ማሰብ የለቦትም። በእንግሊዝ ሃገር ከ16 አመት በታች ከሆኑ ልጆች ጋር ግንኙነት መፍጠር በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የለዉም።

ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ ከሆኑ ምንም አይንት የወሲብ ድርጊት ከማድረጎ በፊት ለአጋሮ መግለጽ ይኖርቦታል። ይህንን ካላደረጉ የወንጀል ክስ ይቀርብቦታል። ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ መሆን የጥገኝነት ማመልከቻዎን አይጎዳም፤ ከእንግሊዝም እንዲባረሩ አያስደርግም።

በሴተኛ አዳሪነት እና በወሲብ ንግድ የተሰማሩ ስዎች ያሉበት አካባቢ ሊኖሩ ይችላሉ ነግር ግን እነዚህ ስዎችን በአደባባይ ለወሲብ መጠየቅ ህግ ወጥ ተግባር ነዉ ፤ ይህ በእንግሊዘኛዉ ከርብ ዋኪንግ ይባላል። በሴተኛ አዳሪነት ከተሰማሩ ሰዎች ጋር ላለማዉራት ይሞክሩ። ምክኛቱም አለመግባባት ሊፈጠር ስለሚችል እና እራሶን አደጋ ላይ ሊጥሉ ስለሚችሉ።



### አልኮል፣ ሲጋራ እና እፅ

አልኮል ለመግዛት ትክክለኛዉ እድሜ 18 ነዉ። ከ18 አመት በታች ለሆኑ ልጆች አልኮል መግዛት ጥፋት ነዉ። አንዳንድ የህዝብ ቦታዎች ከአልኮል ነጻ የሆኑ ተባለዉ ተሰይመዋል። በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ሲጠጡ ከተያዙ ቅጣት ይጣልቦታል። ከ16 አመት በታች የሆኑ ልጆች ብዙ ካፊን ያለበት ሃይል ሰጪ መጠጦችን ከመጠጣት ታግደዋል።

ሲጋራ ወይም ሲምባሆ ለመግዛት ህጋዊ እድሜዉ 18 ነዉ። ከ18 አመት በታች ለሆኑ ልጆች ሲጋራ መግዛት ጥፋት ነዉ። ሙሉ በሙሉ በታጠሩ ወይም ባብዛኛዉ ዝግ በሆኑ በታዎች ዉስጥ እና ስራ ቦታ ውስጥ ማጨስ ህግ ወጥ ነዉ። ይህ የህዝብ አገልግሎት የሚሰጥባቸዉ እንደ አዉቶቢስ እና ባቡር ያሉ መጓጓዣዎችንም ይጨምራል። ክቬፒንግ ጋር የተገናኘ እገዳ ባይኖርም በስራ ቦታ፣ከሆስፒታል ውጪ እና ህዝብ የሚገለገልባቸዉ ህንፃዎች አካባቢ መጠቀም የተከለከለ ነዉ።

ህገወጥ አደንዛዥ እፆችን ሲጠቀሙ፣ ሲይዙ ወይም ሲሸጡ ከተገኙ ሊታሰሩ ይችላሉ። ከኬሚስት ወይም ከዶክተር የታዘዙሎትን መድሃኒት መያዝ ይችላሉ። ህገወጥ አደንዛዥ እፆች ክላስ ኤ፣ ቢ እና ሲ ተብለዉ ይከፈላሉ፤ ክላስ ኤ አደንዛዥ እፆችን በህግ በጣም አደገኛ ናቸዉ ተብለዉ የሚተፈረጁ ናቸዉ። ካናቢስ በአንዳንድ ሃገሮች ህገወጥ ባይሆንም በእንግሊዝ ግን እንደ ክላስ ቢ አደንዛዥ እፅ የሚታይ ሲሆን ፤ ቤት ዉስጥም ቢሆን መጠቀም ህገ ወጥ ተግባር ነዉ። ጫት በአንዳንድ ሶማሊ ህብረተሰቦች ዉስጥ እንደማነቃቂያ የሚጠቀሙት እጽ ሲሆን በእንግሊዝ ሃገር ህገ ወጥ ሲሆን እንደ ክላስ ሲ እጽ ነዉ የሚታየዉ።



**የእንግሊዝ ሃገር እሴቶች፣ ግዴታዎች፣ መብቶች እና ነፃነቶች**
የእንግሊዝ ሃገር የባህል እሴቶች እና የሃይማኖት ልዩነቶች እና መቻቻል እና እኩልነት ጠቃሚ እሴቶች ናቸዉ። ሃይማኖታዊ ወይም የቀኝ ፅንፈኝነት ወይም ዘረኝነት ተቀባይነት የላቸዉም። ምንም እንኳን ከለመዱት የተለየ ቢሆንም ሰዎች የሌሎችን አስተሳሰብ፣ ሃይማኖት እና አለባበስ ማክበር አባቸው ።

ሃይማኖቶን የማምለክ መብቶት የተጠበቀ ነዉ። ቤተ ክርስቲያኖች፣ መስጊዶች፣ ምኩራቦች ወይም የተለያዩ የአምልኮ ቦታዎች በከተሞች ያገኛሉ።

ሰዎችን በመጡበት ቦታ ምክንት ፣ በፆታቸዉ፣ በወሲባዊ ዝንባሌያቸዉ፣ በሃይማኖታቸዉ፣ በፖለቲካዊ አስተሳሰባቸዉ፣ በእድሜያቸዉ ወይም በአካል ጉዳተኝነታቸዉ ምክንያት በመጥፎ ሁኔታ ወይም በተለየ ሁኔታ መቀበል ህገወጥ ድርጊት ነዉ ፤ እንደ ጥላቻ ወንጀልም ነዉ የሚታየዉ። የጥላቻ ወንጀል መጥፎ ስሞችን መጥራት፣ ጉልበተኝነትን (ቡሊይንግ)፣ ጥቃት፣ ዝርፊያ እና መኪና ወይም ቤትን ማውደም፣ ግራፊቲ ወይም ጽሁፍ እና ትንኮሳን ያካትታል።

የጥላቻ ወንጀል ከተፈፀመቦት በ**101** ቁጥር ለፖሊስ ቀጥታ በመደወል ማመልከት ይችላሉ ፤ እነሱም ጉዳዩን ይመረምራሉ ፤ ድጋፍ እና ምክርም ያሰጦታል።

የወንጀል ሰለባ ሆነዉ የስነ ልቦና እና የአካላዊ ድጋፍ ከፈለጉ ከቪክተም ሰፖርት/የተጎጂዎች ድጋፍ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። ይህ የድጋፍ አገልግሎት ተጎጂዎች ወንጀሉን ለፖሊስ አመልክተዉ ቢሆንም ባይሆንም ድጋፍ ይሰጣሉ። ወንጀልን፣ የጥላቻ ወንጀልንም ጨምሮ ማለት ነዉ ሪፖርት ለማድረግ ከፈለጉ እርዳታ ያደርጉሎታል። በአካባቢዎ ያለዉን ቪክተም ሰፖርት/የተጎጂዎች ድጋፍ ግሩፕ ለማግኘት እባክን የሚገተለዉን ድህረ ገጽ ይጠቀሙ www.victimsupport.org.uk ወይም በነፃ የሚከተለዉን ቁጥር ይጠቀሙ 08081689111.

**አስቁሞ መፈተሽ**
ፖሊሶች በፈለጉት ሰአት አስቁመዉ ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ ነገር ግን ይህ የተለመደ ክስተት አይደለም እናም በየጊዜዉ መከሰት የለበትም። ፖሊስ አስቁሞት ስሞት ማነዉ፣ በአካባቢዉ ምን ይሰራሉ፣ ወዴት እየሄዱ ነዉ ብሎ ሊጠይቆት ይችላል።

ፖሊስ እንደሁኔታዉ ሊፈትሾት ይችላል፣ መፈተሽ ማለት መታሰር ማለት አይደለም። ፖሊስ ህገወጥ እፅ፣ መሳሪያ፣ የተሰረቁ ቁሳቁስ ወይም እንደ ክሮ ባር ያሉ ወንጀል ለመፈጸም የሚያመቹ ነገሮች ይዘዋል ብለዉ ለማመን 'ምክንያታዊ ሁኔታ' መኖር አለበት።


'ምክንያታዊ ሁኔታ' ከሚባሉት ዉስጥ ለምሳሌ ፖሊስ ከኪሶ ወይም ከቦርሳዎት ዉስጥ የሆነ ነገር ተንጠልጥሎ ሲያዩ ወይም ከዚህ በፊት እንደዚህ አይነት ነገሮችን ይዞ ካዩት ሰዉ ጋር አብረዉ ከሆኑ ሊሆን ይችላል።

የፖሊስ ኮሚኒቲ ሰፖርት ኦፊሰር (ፒሲኤስኦ) ሲያስቆሞት ዩኒፎርም መልበስ አለበት። አንዳንድ ግዜ ፖሊሶች ምልክት የሌለዉ መኪና ውስጥ ሊሆኑ ይችላልሉ እንዲሁም ፖሊስ ኦፊሰሩ ሁሌ ዩኒፎርም ላይለብስ ይችላል ነገር ግን ዩኒፎርም ካልለበሱ የማዘዥ ካርዳቸዉን (ዋረንት ካርድ) ማሳየት አለባቸዉ።



አስቁሞ የመፈተሽ ሂደቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ አይደለም – ህጉ ፖሊስ አስቁሞ እንዲፈትሽ ስልጣኑን ሰጥቶታል እናም ፈቃደኛ ካልሆኑ በሃይል ሊፈትሹ ይችላሉ።

**ፖሊስን ማግኘት**



ፖሊስን ለማግኘት ወደየትኛዉም ፖሊስ ጣቢያ መሄድ ወይም 24 ሰአት በስልክ ማግኝት ይችላሉ።

ብዙ አጣዳፊ ላልሆነ ጉዳይ 101 ላይ በመደወል ፖሊስን ማግኘት ይቻላል ለምሳሌ ንብረቶት ከተጎዳ፣ ስለወንጀል መረጃ ለመስጠት ወይም መረጃ ለማወቅ ከፈለጉ።

አጣዳፊ ያልሆኑ ወንጀሎችን ለፖሊስ ኦንላይን ላይ ቀለል ያለ ፎርም በመሙላት ማመልከት ይችላሉ። ኢንተርኔት ላይ የአካባቢዎን የፓሊስ ኦንላይን ሪፖርት ፎርም ፈልገዉ መጠቀም ይኖርቦታል።

አጣዳፊ ጉዳይ ካጋጠሞ 999 ይድዉሉ ፤ ለምሳሌ የጥቃት ሰለባ ከሆኑ ወይም ወንጀል ሲፈፀም ካዩ። ሲደዉሉ 'ፖሊስ' እንደሚፈልጉ ይናገሩ ምክንያቱም ቁጥሩ ለአንቡላንስ ወይም ለእሳት አደጋ መጥሪያም ስለሚጠቀሙበት ነዉ። 999 የስልክ መስመር በነፃ የሚጠቀሙት መስመር ነዉ።

999 ሲደዉሉ አስተርጓሚ ካስፈለጎት ስልኩን አይዝጉት። ምን ቋንቋ እንደሚፈልጉ ይናገሩ። መስመሩ (እስከ 10 ደቂቃ) ዝም ሊል ይግላል ከዘም ቋንቋዎትን የሚናገር ሰዉ ሊረዳዎት ይቀርባል። አጣዳፊ ከሆነ እና ስልክ ላይ መቆየት ካልቻሉ ያሉበትን መንገድ ስም ይናገሩ እና ፖሊስ ወደ እዛ ይመጣል።

የሚከተሉትን መማር ይረዳል:

- ፖሊስ እንዴት መጠየቅ እንዳለቦት
- በእንግሊዘኛ አድራሻዎን መናገር ማወቅ
- አድራሻዎ ላይ ካልሆኑ በአካባቢዉ ያሉትን ምልክቶች በማየት ያሉበትን ማሳወቅ ለምሳሌ የሱቅ ወይም የመንገድ ስም መናገር
- የትኛዉን ቋንቋ እንደሚናገሩ ማሳወቅ

እንግሊዝ ሃገር ዉስጥ ፖሊሶች ከህግ በላይ አይደሉም፣ ቅሬታ ካሎት እነሱ ላይ ማመልከት ይችላሉ። ፖሊስ ኦፊሰር ላይ ወይም የፖሊስ ስታፎች በወሰዱት እርምጃ ላይ ቅሬታ ካሎት ማመልከት ይችላሉ። ይህንን የትኛዉም ፖሊስ ጣቢያ ወይም 101 ላይ በመደወል ወይም የአካባቢዎን የፖሊስ ድህረ ገጽ በመጠቀም ማመልከት ይችላሉ።